የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ—የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 37
ADDIS ABABA - 9th February, 1999

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፶፯/፲፱፻፺፩ ዓ·ም·
ከኩዌት መንግሥት ጋር የተደረገ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ............... ገጽ ፱፻፹፭

## CONTENTS

Proclamation No. 157/1999
The State of Kuwait Air Transport Services Agreement Ratification Proclamation ... Page 985

### አዋጅ ቁጥር ፩፻፶፯/፲፱፻፺፩
### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት መንግሥት መካከል የተደረገውን የአየር አገልግሎት ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት መንግሥት መካከል እ·ኤ·አ ኦክቶበር ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፰ ኩዌት ላይ በመፈረሙ፤

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው ተዋዋዮቹ አገሮች ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መዋዋልና ተፈጻሚ ማድረግን በተመለከተ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቶቻቸው መፈጸማቸውን በዲፕሎማቲክ መስመሮች በመጨረሻ ከተገላለጹበት ወር የመጀመሪያው ቀን ጀምሮ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «ከኩዌት መንግሥት ጋር የተደረገ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፶፯/፲፱፻፺፩» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO.157/1999
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AIR TRANSPORT SERVICES AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE STATE OF KUWAIT

WHRREAS, an Air Transport Services Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Kuwait was signed in Kuwait on the 26th day of October, 1998;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall come into force on the first day of the month from the date of the last notification, through diplomatic channels, of the completion of the respective constitutional formalities of the contracting parties, concerning the conclusion and implementation of international agreements;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 9th day of February, 1999;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This proclamation may be cited as the "State of Kuwait Air Transport Services Agreement Ratification Proclamation No. 157/1999."

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት መንግሥት መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፰ ኩዌት ላይ የተፈረመው የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት ጸድቋል።

፫· <u>የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ሥልጣን</u>

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ፣ የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

The Air Transport Services Agreement signed in Kuwait on the 26th day of October, 1998 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Kuwait is hereby ratified.

3. *Power of the Minister of Transport and Communications*

The Minister of Transport and Communications is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 9th day of February, 1999.

Done at Addis Ababa, this 9th day of February, 1999.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE